# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 103 ሚያዚያ 28 ቀን 2002 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላከያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ክሪስ ፍላኸርቲ የተባሉ አሜሪካዊ በዋይት ሃውስ ፊት ለፊት ብርትኳን ትፈታ በሚል የረሃብ አድማ ላይ እንደሚገኙ ተዘገበ

ክሪስ ፍላኸርቲ የተባሉ አሜሪካዊ የኪነ-ጥበብ ሰው በአሜሪካው ቤተመንግስት ፊት ለፊት በኢትዮጵያ ለሰብዓዊ መብት መከበር እና ለወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ መፈታት ሲሉ በረሃብ አድማ ላይ እንደሚገኙ ተዘግቧል።

ሰኞ ሚያዝያ 25 ቀን በዋሽንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ከቀትሩ ስምንት ሰዓት ላይ አድማቸውን የጀመሩት ሚስተር ፍላኸርቲ፣ ፕሬዘደንት ባራክ ኦባማ ወይም የአስተዳደራቸው ባለስልጣን ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ የህሊና እስረኛ መሆናቸውን በማመን መግለጫ እስኪሰጡ ድረስ የመቀጠል አላማ እንዳላቸው ተናግረዋል። ባራክ ኦባማ ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ እንዲፈቱ ጥሪ እንዲያቀርቡም ጠይቀዋል።

ሚስተር ፍላኸርቲ ወደ አድማው የገቡባቸውን ሶስት ዋና ምክንያቶች ሲገልጹ፥ የባራክ ኦባማ አስተዳደር ወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ የህሊና እስረኛ መሆናቸውን እንዲቀበል፤ በአሜሪካን አገርና በአለም ዙሪያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወ/ት ብርትኳንን ነፃነት ለማቀዳጀት በሚደረገው ጥረት የግል ተሳትፎ እንዲያደርጉ ጥሪ ለማድረግ፤ እንዲሁም በታሰሩበት ወቅት እራሳቸውም በረሃብ አድማ ላይ ለነበሩት ለወ/ት ብርትኳን ሚደቅሳ ድጋፍ እና ርህራሄ ለማሳየት ነው ብለዋል።

የሚስተር ፍላኸርቲን ጥረት በማሞገስ እና ድጋፋቸውን በመግለጽ የተለያዩ የኢትዮጵያውያን ሲቪል ቡድኖች መግለጫ ማውጣታቸውን ቀጥለዋል።

## ባራክ ኦባማ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች መረጃን በነፃነት የማግኘትን መብት እየገቱ ነው ሲሉ አወገዙ

ባራክ ኦባማ ሰኞ ሚያዝያ 25 የአለም አቀፍ የፕሬስ ነፃነትን ቀን በሚመለከት በሰጡት መግለጫ ላይ፣ እንደ ቻይና እና ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች የዜጎቻቸውን መረጃ የማግኘት መብት እየገቱ ነው ብለዋል።

የሰው ልጆች ከምን ጊዜውም በበለጠ መረጃ ሊያገኙ የሚችሉባቸው እንደ ኢንቴርኔት፣ ተንቀሳቃሽ ስልኮች እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን የማግኘት እድላቸው ከፍ ባለበት በዚህ ጊዜ እነዚህ አገሮች ግን የተሟላ የመረጃ ፍሰት እንዳይኖር እያገቱ መሆናቸውን ኦባማ በመግለጫቸው አስቀምጠዋል።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ የሚያቀርበው የኢንተርኔት አገልግሎት ሆነ ተብሎ ዋጋው የተወደደ ከመሆን ጀምሮ ጥራቱም በጣም ዝቅ ያለ ሲሆን፤ ይህንና የስልክ አገልግሎቱን የአፈና መዋቅሩ አካል ማድረጉም ይታወቃል። በተጨማሪም፥ መረጃ በቀጥታ ለህዝብ የሚያቀርቡ መገናኛ ብዙሃንን በተለያዩ አቅጣጫዎች ሲያጠቃ የቆየ ሲሆን፤ በቅርቡ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮን ማፈኑን አምኗል።

## የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የወያኔን የግብር ስርአት እያማረሩ ነው

ባለፈው ሳምንት የግብር ስርአቱን አስፈላጊነት ለህዝብ ማስተዋወቅ በሚል የወያኔ ካድሬዎች ባብዛኞቹ የአዲስ አበባ ቀበሌዎች በጠሩት ስብሰባ ላይ ነዋሪዎች ስሞታቸውን ማሰማታቸውን ዘጋቢያችን ከስፍራው በላከው መረጃ አስታውቋል።

ነዋሪዎቹ፥ ከሚከፈለው መጠን ጀምሮ እስከ አሰባሰብ ሂደቱ፣ የግብር ስርአቱ ኢ-ፍትሃዊ መሆኑን አማረዋል። አንዳንዶችም፣ ካድሬዎች እና ዘመዶቻቸው ግብር እንደማይከፍሉ እና ዜጎች የሚከፍሉት ግብር መጠንም በዝምድና ላይ የተመሰረተ ነው ሲሉ ተቃውሟቸውን ገልጸዋል። ትናንሽ የመንደር ንግዶች ሳይቀሩ ከአቅማቸው በላይ የሆነ ግብር እንዲከፍሉ መደረጋቸውንም አስመልክቶ ነዋሪዎቹ ምሬታቸውን መግለፃቸውን ዘጋቢያችን ያስተላለፈው መረጃ አስረድቷል።

# ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

በአሁኑ ጊዜ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የግብር ስርአቱን ለፖለቲካ ጉዳይ ማስፈጸሚያነት እየተጠቀመ መሆኑ በሰፊው የሚነገር ሲሆን፤ አንዳንድ ከአገዛዙ ጋር ያልተግባቡ ነጋዴዎችም ግብር አልከፈላችሁም በሚል ክስ ለእስር እየተዳረጉ እንዳሉ ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል።

## በአዲስ አበባ እና በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የመብራት እጥረት ዜጎችን ለእንግልት እየዳረገ ነው ተባለ

የኤሌክትሪክ ሃይል መጥፋት ህዝቡን ለተጨማሪ እንግልት እየዳረገው መሆኑን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው መረጃ አስታውቋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አንዳንድ አካባቢዎች በቀን እስከ 16 ሰዓታት ድረስ የመብራት ሃይል የማይኖርበት ጊዜ ያለ ሲሆን፤ በምእራብ ኢትዮጵያ የአንዳንድ ዞኖች ነዋሪዎችም ለረጅም ጊዜ ያለመብራት መቆየታቸውን ለዘጋቢያችን ገልጸዋል። እንደ አንዳንድ ምንጮች መረጃ፣ በአገሪቱ ተጠቃሚ ከሆነው አካባቢ ቢያንስ ግማሽ ያህሉ በአሁኑ ሰአት የሚኖረው በጭራሽ ያለ ኤሌክትሪክ ሃይል ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፥ የአዲስ አበባ የወያኔ ካድሬዎች በምረጡን ዘመቻቸው ላይ አገዛዙ ለከተማይቱ ነዋሪዎች የ24 ሰዓት የመብራት ሃይል እንዳቀረበ እንደሚናገሩ ለማወቅ ችለናል።

## በአዲስ አበባ ከተማ ወያኔን ምረጡ በሚል በአደባባይ ምግብ ሲያከፋፍሉ የነበሩ ባለስልጣናት በመንገድ አላፊዎች ተሰደቡ

ባለፈው አርብ ሚያዝያ 22 ቀን በተለምዶ የጦር ሃይሎች አደባባይ በሚባለው ቦታ ለአካባቢው ነዋሪዎች ምግብ እየሰጡ የምረጡን ዘመቻ ሲያደርጉ የነበሩ የወያኔ ባለስልጣናት እንደተሰደቡ ለማወቅ ችለናል።

የወያኔ ሹመኞች የሆኑት የክፍለ ከተማ አመራሮች፣ እንደተለመደው በቀበሌ ካድሬዎች ጫና አማካኝነት ከቤት አስወጥተው አደባባዩ ላይ እንዲገኙ ላደረጓቸው እናቶች ዳቦ እየቆረሱ በመስጠት እና ቆሎ በማስዘገን ገዢውን ፓርቲ እንዲመርጡ ተማጽነዋል።

በወቅቱ የአውቶብስ ላይ ተጓዦችን ጨምሮ በአካባቢው ሲያልፉ የነበሩ ሰዎች "ሌቦች ሌቦች!" የሚል ጩኸት በማሰማት የወያኔን ባለስልጣናት ሲሳደቡ እነደነበርም በስፍራው የነበሩ ምንጫችን ካስተላለፉልን መረጃ ለመረዳት ችለናል።

## ጠበቃ ሚሊዮን አሰፋ በመጪው የምርጫ ተውኔት በፍቼ ከተማ ወያኔን ወክሎ የሚወዳደረው ገጸ ባህሪ መሆኑ ታወቀ

የወያኔ ምርጫ ቦርድ እና የቴዲ አፍሮ ጠበቃ የሆነው ሚሊዮን አሰፋ በፍቼ ከተማ ወያኔን ወክሎ በመጪው ግንቦት የምርጫ ተውኔት እንደሚጫወት ታውቋል።

ሚሊዮን አሰፋ ከዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ጋር ጥብቅ ግንኙነት እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን፤ የተለጣፊው የኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበር መስራች መሆኑንም ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል። ከ1997 ምርጫ በኋላ የቅንጅት ፓርቲ ጠበቆች የወያኔን ምርጫ ቦርድ ሲከሱ፤ ሚሊዮን አሰፋ እና የዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ጠበቃ መብራህቱ ቦርዱን በመወከል ቆመው ነበር።

ግለሰቡ የቅንጅት አመራሮች ከመታሰራቸው በፊት ሙያዊ አስተያየቱን እንዲሰጥ በሚል ቴሌቪዥን ላይ ቀርቦ ወንጀለኞች ናቸው ሲል መናገሩ ይታወሳል። ነፃውን ፕሬስ የሚመለከተውን አፋኝ ህግና ኢትዮጵያውያን ዜጎችን በፍርሃት ስር ለማኖር የወጣውን የወያኔ ጸረ-ሽብር ተብዬ ህግ ያረቀቁትም ይኸው ሚሊዮን አሰፋ እና የበረከት ስምኦን ምክትል ዋሾ የሆነው ሽመልስ ከማል ናቸው።

በባህርዳር በተደረገው የገዢው ፓርቲ ጉባኤ ላይ የአየር ቲኬት እና የሆቴል ወጪው በአገዛዙ ተሸፍኖ በክብር እንግድነት መገኘቱን በአዲስ አበባ ለሱ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ከላኩት መረጃ ለማወቅ ችለናል። ከዛም በኋላ መቀሌ በተደረገ ሌላ ስብሰባ ላይ ከሽመልስ ከማል ጋር በክብር እንግደኝነት የተገኘው ሚሊዮን፤ በአሁኑ ሰዓት ከወያኔ ጋር ቅርበት ላላቸው ባለሃብቶች የጥብቅና አገልግሎት በመስጠት ሃብት እያካበተ እንዳለም እነዚሁ ምንጮች አሳውቀውናል።

ሚሊዮን አሰፋ ከዘረኛው አገዛዝ ጋር በመወገን የሚሰራበትን ምክንያት ለማወቅ በሚል ጥያቄ የላክንላቸው እና ግለሰቡን በቅርብ የሚያውቁት ሰው፤ "ሚሊዮን አሰፋ ስልጣን ፈላጊ እና አድር ባይ ነው፤ ብቸኛ ምክንያቱ ይኸው ነው" ብለውናል።

## በወያኔ የአፈና ሥርዓት ውስጥ ስለልማት ማውራት ቅጥፈት የተሞላበት ቧልት ነው!!!

ደርግ "አብዮታዊ" የተሰኘውን ቃል ይወድ እንደነበር እናስታውሳለን። ወያኔ ደግሞ "ልማታዊ" ከሚለው ቃል ጋር ፍቅር ይዞታል። ልማታዊ አስተሳሰብ፣ ልማታዊ ቢሮክራሲ፣ ልማታዊ ፓለቲካ፣ ልማታዊ ባለሃብት፣ ልማታዊ ጋዜጠኛ፣ ልማታዊ መንግሥት፣ ... ዝርዝሩ መጨረሻ የለውም። ደርግ "አብዮታዊ" የተባለውን ቃል መደጋገሙ አብዮታዊ እንዳላደረገው ሁሉ ወያኔም "ልማታዊ" የተሰኘውን ቃል መደጋገሙ ልማታዊ አያደርገውም።

የወያኔ የፈጣን ልማት ክርክሮች የተለመዱ የውሸት ቁልሎች መሆናቸው ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግልጽ ቢሆንም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አንዳንዴ ጆሮዓቸውን ጣል ለሚያደርጉላቸው ወገኖቻችን የሚከተሉትን ነጥቦች ማስታወስ እንሻለን።

1. የወያኔ ስታትስቲክስ ከእውነታ ጋር አንዳችም ተዛምዶ የሌላቸው ቢሮ ውስጥ የሚሞሉ የውሸት ቁጥሮች ናቸው። ወያኔ እነዚህን ቁጥሮች የሚፈልጋቸው ለውሸቱ ማጠናከሪያነት ብቻ ነው። ለምሳሌ የሕዝብ ብዛት በአንፃራዊ መልኩ ውስብስብነት የሌለው የስታትስቲክስ መረጃ ነው። እኛ ግን ቁጥራችን እንኳን ሳይቀር በወያኔ ውሳኔ ተዛብቶ ስንት መሆናችንን መገመት የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ቁጥራችንን እንኳን ሊነግረን ያልፈቀደ መሥሪያ ቤት የገበሬውን ማሳ በትክክል ለክቶ፤ ምርታማነትን አስልቶ፤ እውነቱን ይነግረናል ማለት ዘበት ነው። የወያኔ የስታትስቲክስ ባለሥልጣን ሠራተኞች መ/ቤታቸውን "የቁጥሮች መቀቀያ ቶፋ" ብለው የሚጠሩት ያለምክንያት አይደለም። እነዚህ ሠራተኞች አንድ ቀን እንደ አርጀንቲና አቻዎቻቸው "ቁጥር መቀቀል ሰለቸን፤ በማስዋሸት ከፈጣሪያችን አታጣሉን" ብለው በጋራ የማመጽን ድፍረት ያገኙሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን የወያኔን ስታትስቲክስ ወደ ቆሻሻ መጣያ ቅርጫቶች ከመላክ የተሻለ አማራጭ የለም።
2. የዓለም ባንክና የዓለም የገንዘብ ድርጅት የራሳቸውን መረጃ አይሰበስቡም። እንደዚያማ ቢሆን ኖሮ ሥራቸው በዓለም አገሮች ሁሉ መረጃ መሰብሰብ ብቻ በሆነ ነበር። ሥራቸው ይህ አይደለም። ድርጅቶቹ የሚጠቀሙት የየአገሩ መንግሥታት የሰጧቸውን ቁጥሮች ነው። ኢትዮጵያንም በተመለከተ የጥናታቸው መነሻዎች ያው የወያኔ የስታትስቲክስ ባለሥልጣን የሚሰጣቸው ቁጥሮች ናቸው። ገለባ ከገባ የሚወጣውም ገለባ ነውና በተዛባ መረጃ መነሻነት የሚያደርጉት ጥናት እተዛባ መደምደሚያ ላይ እንደሚያደርሳቸው ጥርጥር የለውም። እናም መለስ የሰጣቸውን ቁጥሮች አማስለው ያመጡትን ውጤት እንደ አዲስ ግኝት እየተቀበለ ፍጹም በሆነ አይን አውጣ ድርቅና "ይኸው ያስመዘገብኩት ፈጣን እድገት በውጭ ባለሙያዎችም ተረጋግጧል" ይለናል።
3. የወያኔ የውሸት ፋብሪካ በአደናጋሪ ሥራዎች የሚደገፍ በመሆኑ አንዳንዶቹ ነገሮች ጥንቁቅ ያልሆነ ባለሙያን ሊያዘናጉ ይችላሉ። ለምሳሌ በርካታ አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች መከፈታቸው እውነት ነው። ሆኖም አዳዲስ የተከፈቱት ዩኒቨርስቲ ተብየዎች የዩኒቨርስቲ መስፈርት የማያሟሉ መሆናቸው፤ አንዳንዶቹ ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትነት እንኳን የማይበቁ መሆናቸውን ብዙዎች ላያውቁ ይችላሉ። የከተማ ህንፃዎችም እንደዚያው ናቸው። ህንፃዎች ሲገነቡ ይታያሉ፤ የህንፃዎቹ ባለቤቶች ግን ራሳቸው ወያኔዎች ስለመሆናቸው አይነገርም። ብዙ የሚወራለት የመንገዶች ግንባታም ሙሉ በሙሉ በብድርና በእርዳታ የሚደረግ ስለመሆኑም አይነሳም።
4. ወያኔ ራሱን የሚያነፃፅረው ከደርግ ጋር መሆኑ ሌላው የማወናበጃ ስልት ነው። የደርግ ሥርዓት ከተወገደ ሁለት አስርት ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም ወያኔ ስልጣን ላይ የወጣው ሃቸ አምና እንደሆነ አስመስሎ ያወራል። በሃያ ዓመታት ውስጥ የት መድረስ ይቻል ነበር የሚለው ጥያቄ እንዲነሳ አይፈልግም። ከዚህም በተጨማሪ ሁለቱ ሥርዓቶች የኖሩት እጅግ በተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ሁኔታዎች መሆኑን እንድንዘነጋለት ይፈልጋል። ሌላው ሁሉ ቢቀር ወያኔ የደርግን አስር ጊዜ እጥፍ የሚሆን የውጭ አገራት የልማት እርዳታ የሚያገኝ መሆኑ ተሳስቶም እንኳን አያነሳውም፤ እንዲነሳም አይፈልግም።
5. ወያኔ ሥራውን ከሌሎች የአካባቢው አገሮች ጋር ማነፃፀርም አይፈቅድም። ዘወትር ስለ ኢትዮጵያ ተዓምራዊ ልማት ሲያወራ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ባሉበት የቆሙ ያስመስላቸዋል። በተቻለው መጠን ራሱን ፈጽሞ ከማይመስሉት ከቻይናና እሩቅ ምሥራቅ አገሮች ጋር ማወዳደር ይሻል፤ በዚህም ምክንያት ጎረቤት አገሮች እያስመዘገቡት ያለው ልማት እንዳይታይ ያደርጋል። እንደ እውነቱ ከሆነ ያለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በርካታ የአፍሪካ አገሮች ጥሩ የተባለ እድገት ያሳዩባቸው ጊዜዓት ናቸው፤ ለዚያውም የውሸት ክምር ባልሆነ ተዓማኒ መረጃ መሠረት። ይህንን ውጤት ለማስመዝገብ አገራቱ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" የሚባል መተት አላስፈለጋቸውም።
6. ልማት እንጀራ መጋገር ብቻ አይደለም፤ የጋገሩትን እንጀራ የመብላትንም መብት ያጠቃልላል። ማን ምንያህሉ ቁራጭ ደረሰው የሚለውም ይታሰባል። ከዚህም አልፎ ነገ እንጀራ የማግኘት ተስፋንም አሻግሮ ይመለከታል። ልማት በቁሳዊ ሃብቶች ብቻ ሳይሆን ቁሳዊ ባልሆኑ ሃብቶችም ጭምር ይለካል። ልማት የዛሬ ነፃነትንና የነገንም ተስፋ ያጠቃልላል። ወያኔ እስከዛሬ ከነበሩ አፋኝ ሥርዓቶች ሁሉ የባሰ ፀረ-ልማት ኃይል መሆኑን ግልፅ ስለሚያደርግ ይኸንን የተሟላ የልማት ትርጉም ከመዝገበ ቃላታችን መፋቅ ይሻል። በተቻለው መጠንም ዓይኖቻችን ግዑዝ ነገሮች ላይ ብቻ እንዲያተኩሩና ስለ መንፈሳዊ ሃብቶቻችን፣ ስብዕናችን፣ ክብራችን፣ አንድነታችን፣ አገራችን፣ ድንበራችን፣ ነፃነታችን እንዳናስብ ይሻል።
7.

ለመሆኑ ወያኔ ይኸንን የተንሸዋረረ የልማት አጀንዳ ይኸን ያህል ማስጮህ ለምን አስፈለገው? መልሱ አጭር እና ግልጽ ነው። በአሁኑ ሰዓት በሥልጣን የመቆያዬ ብቸኛ ቅቡል ምክንያት "ልማታዊ መንግሥት" መሆኔ ነው ብሎ አምኗል። ዘረኝነቱ፣ ማፍያነቱና ሽፍታነቱ ከመቸውም በላይ ገሃድ እየሆነ በመምጣቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ መጠላቱ ምርጫ 97 በማያሻማ ሁኔታ አሳይቶታል። አሁን አለኝ የሚለው ብቸኛው መንጠላጠያው እና "ምርጫ 2002" ለተሰኘው ድራማ ወያኔ ይዞ የመጣው ብቸኛ መከራከያ "ልማታዊ መንግሥት" ነኝ የሚለው አሰልቺ ንዝንዝ የሆነው ለዚህ ነው። የወያኔ የክርክር ጭብጥ "እንጀራ እስከሰጠሁህ ድረስ ረግጬ ልገዛህ መብቴ ነው" እንደማለት ይቆጠራል። ይህን የሚለው ደግሞ የሚሰጠው እንጀራ ሳይኖር መሆኑ ክርክሩን መራር ምፀት ያደርገዋል። የወያኔ የልማት ዲስኩር ትንሽ እንኳን እውነት የሌለው መሆኑን ከማንም በላይ ራሱ ወያኔ ያውቃል። ለዚህም ነው ምርጫን "ለማሸነፍ" መሸመቅ፣ ማድፈጥ፣ ማገት፣ ማንገላታት፣ ማፈን፣ ማስፈራራት፣ መግደል ያስፈለገው።

የወያኔ የነጋ ጠባ "ልማታችን፣ ልማታችን" የቁራ ጩኸት እንዲህ ሃቅን ለማድበስበስ ታስበው በተፈበረኩ ቁጥሮች እና በጥቂት የታይታ ሥራዎች የቆመ የእንቧይ ካብ ነው። ሃቁ ኢትዮጵያችን ውስጥ ድህነትና ሥራ አጥነት በዝቷል፤ የመኖሪያ ቤት እጥረት ተባብሷል፤ በሽታዎች ተስፋፍተው ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ ነው፤ የትምህርት ጥራት አሳፋሪ ደረጃ ላይ ወድቋል፤ ስደት ተሰምቶ ወደማይታወቅ ደረጃ ደርሷል፤ሙስና ተቀባይነት ያለው አሠራር ሆኗል። በመብቶች ረገድ ደግሞ ኢትዮጵያ ጥቂት ወንበዴዎች ሕዝቦቿን ያገቱባት ትልቅ እስር ቤት ሆናለች። ይባስ ብሎ ወያኔ ከኔ የተሻለ አሳሪ አታገኙም እያለ ይሳለቅብናል።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ወያኔ በልማት ስም የሚነዛውን ውዥንብር እየተከታተለ ያጋልጣል። በወያኔ የአፈና ሥርዓት ውስጥ ስለልማት ማውራት ቧልት ብቻ ሳይሆን ቅጠፈት መሆኑንም አስረግጦ ይናገራል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፣ ቁጥር 103 ሚያዚያ 28ቀን 2002 ዓ.ም፣

# እስከዛሬ ድርጅቶቻችን ውጤታማ ለምን አልሆኑም? ግንቦት7ስ በምን ይለያል?

ታደሰ ብሩ  አፕሪል 10  2010 ሙኒክ ላይ  በተካሄደ ህዝባዊ ስብሰባ የቀረበ ንግግር **ክፍል 1**

ክቡራትና ክቡራን በዛሬው እለት በመካከላችሁ ተገኝቼ የእስካሁን የድርጅት ልምዶቻችንን በተመከለተ ያለኝን ጥቅል ሃሳብ እና ስለ ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቂ ድርጅታዊ ይዘት እንድናገር እድል ስለተሰጠኝ ከልብ አመሰግናለሁ። የዛሬ ሶስት ሳምንት ኦስሎ ውስጥ “ወደፊት መራመድ እንዴት አቃተን?  ለወደፊቱስ ምን ማድረግ እንችላለን?” በሚል ርዕስ ባለፉት ሃምሳ አመታት ጊዜ ውስጥ የረባ ለውጥ ለማምጣት ያልቻልንባቸው ምክንያቶች ናቸው ብዬ የማምንባቸውን ሰባት ነጥቦችን አንስቼ ነበር። ያ ንግግሬ ያተኮረው እኛ ኢትዮጵያዊያን በግለሰብ ደረጃ ባሉብን ችግሮች እና ችግሮቹንም ለማስወገድ ይጠቅሙን ይሆናል ብዬ ባሰብኳቸው ጉዳዮች ላይ ነበር።

የዛሬው ንግግሬ የዚያው ተከታይ ቢሆንም ትኩረቴ ግን ድርጅት ግንባታ ላይ ይሆናል። ለለውጥ የግለሰብ ተነሳሽነት አስፈላጊ ቢሆንም እንኳን ማኅበራዊ ለውጥ በአንድ ወይም በጥቂት ግለሰቦች ጥረት ብቻ አይመጣም። *“አንድ” ታላቅ ውጤት ለማስገኘት የማይበቃ በጣም ትንሽ ቁጥር ነው ይባላል* / one is too small a number to achieve greatness/ ለታላቅ ውጤት መተባበር ግዴታ ነው። ሆኖም ግን መተባበርን በቅስቀሳ፣ በሰበካና በልመና የምናመጣው ነገር አይለም። ሰዎች መተባበር የማይፈልጉባቸው በርካታ ምክንያቶች አሉ። ዛሬ እነሱ ውስጥ አልገባም።

ዛሬ ልናገር የምፈልገው ብዙ ቅን አሳቢ መካሪዎች የሚረሱትን ነገር ነው። ሰዎች እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን የሚያስተባብሩበት ድርጅት ካልፈጠሩ በጋራ የመሥራት አስፈላጊነት መቀበላቸው ብቻውን እምብዛም ፋይዳ የለውም። ችግሩ ድርጅት በመፍጠር ላይም አያበቃም። የሚፈጠረው ድርጅትም የታለመውን እቅድ ማሳካት የሚችል ውጤታማ ተቋም ማድረግ ከባድ ሥራ ነው። እንዲያውም እኛ ኢትዮጵያዊያን ድርጅትን በተመለከተ የገጠመን ዋነኛ ችግር ይህ ነው ብዬ አስባለሁ። በጋራ ለመሥራት ተስማምተን የመሠረትናቸው ድርጅቶች አይናችን ስር ሲሽመደመዱ አንዳዶቹም ሲፈረካከሱ እናያለን። ስለሆነም “እንደምን ጠንካራ ድርጅት መፍጠር እንችላለን?” በሚል ርዕስ ጉዳይ ላይ መወያየት በጣም ጠቃሚና ወቅታዊም ነው ብዬ አምናለሁ።

ድርጅት ወደ አንድ የፈለግንበት ግብ መድረሻ መሣሪያ እንጂ በራሱ ግብ አይደለም። ድርጅት እንደ መኪና ከአንድ ቦታ ወደ ምንፈልገው ሌላ ቦታ በፍጥነት እንድንደርስ ያግዘናል። ክፋቱ አንዳንዶች ተሳፋሪዎች ልባቸው እመድረሻቸው ላይ ይሆንና ለጊዜው የሚገኙት መኪና ውስጥ መሆናቸውን ይረሱታል። ሌሎቹ ደግሞ የመኪናውን ጉዞ የዘወትር ሕይወታቸው ያደርጉታል። አንድ ለለውጥ የተዘጋጀ ድርጅት አባል ሁለቱንም ዓይነት ተሳፋሪዎች መምሰል የለበትም።

የመጀመሪያዎቹ መኪና ውስጥ መሆናቸውን መርሳታቸው አሰቡበት ከመድረስ ሊያግዳቸው ይችላል። የሚጓዙበትን መኪና ባግባቡ መፈተሽ፣ መጠራረግ፣ መጠጋገን፣ ቅባትና ነዳጅ መስጠት ያስፈልጋል፤ ከሁሉም በላይ ብቃት ባለው አሽከርካሪ መኪናው በጥንቃቄ መነዳት አለበት። አለበዚያ መኪናው ሊሰናከል ይችላል፤ ከከፋም መጥፊያቸው ሊሆን ይችላል። ድርጅትም እንደዚሁ ነው። አንድ ድርጅት አባላቱ አሰቡበት እንዲያደርሳቸው በየጊዜው መፈተሽ፣ መጠረግ፣ መጠገን እና መወልወል አለበት። ከሁሉም በላይ ደግሞ ድርጅቱ ብቃት ያለው አመራር ማግኘቱ መረጋገጥ ይኖርበታል። አለበዚያ ድርጅቱ አባላቱን አሰቡበት ማድረስ አይችልም።

የመኪናውን ጉዞ የዘወትር ሕይወታቸው ያደረጉት ደግሞ የሚጓጉለት የተለየ መድረሻ የለምና መኪናው ሲዞር ቢከርም ችግር የለባቸውም። እነሱ ወይ ሾፌር፣ አለያም ረዳት፣ ወይም ዝም ብሎ ተሳፋሪ ብቻ በመሆን የዘወትር ኑሮዓቸውን መኪና ውስጥ ይኖራሉ። ድርጅትም ውስጥ እንደዚሁ ነው። ዓላማን ማሳኪያ መሣሪያ ወይም መታገያ በመሆን ፋንታ ድርጅትን ኑሮዓቸው ያደረጉ ሰዎችም አሉ። አንዳንዶች እድሜ ልካቸውን መሪ፤ ሌሎች ደግሞ እድሜ ልካቸውን ተመሪ ሆነው ይኖራሉ። ድርጅቱ አንዳችም ውጤት ባያስገኝ አይከፋቸውም - ድርጅታቸው መደበሪያቸው ነው።

እኛ ኢትዮጵያዊያን ስለ ድርጅት ያለን እውቀትና  ልምድ በጣም፣ እጅግ በጣም ውስን ነው። የፖለቲካ ፓርቲዎች የመደራጀታቸው ዜና ተወርቶ ሳይጠገብ የመሰነጣጠቃቸው መርዶ ይከተላል። በአለፉት አርባ አመታት ፓርቲዎች በአንድ በኩል እርስ በርሳቸው ሲበላሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ታርቀው ሲሰባሰቡ እና መልሰው ተጣልተው ሲፈረካከሱ ቆይተዋል። “ኢትዮጵያዊያን አብረን መብላት እንጂ አብረን መሥራት አንችልበትም” የሚለውን አባባል እኔ በበኩሌ እስኪሰለቸኝ ሰምቸዋለሁ። በአንድ ስብሰባ ላይ “ኢትዮጵያ በሩጫ ክብረ ወሰኖችን እየያዘች ለምን በእግር ኳስ ወደኋላ ቀረች?” ተብሎ ለተነሳው ጥያቄ አንዱ የሰጠው ምላሽ

> *በሩጫ በመጀመሪያዎቹ ዙሮች ከተደጋገፍክ ትልቅ ነገር ነው የፍፃሜው ዙር ላይ ግን ሩጫ የግል ነው። ይህ ለኢትዮጵያዊያን ይመቻል። እግር ኳስ ግን ጎሏ ሥር እንኳን ሆነን ካንተ የተሻለ እድል ላለው ጓደኛህ ማቀበል አለብህ። ደግሞም እስከ መጨረሻዋ ሰከንድ ከቡድን ጓደኞችህ ጋር መደጋገፍ አለብህ። ይኼ ጨዋታ ለኢትዮጵያዊያን ፈፅሞ አይመችም* - የሚል ነበር።

ይኸንና የመሳሰለውን ስሰማ ‘እኛ ኢትዮጵያዊያን ለተደራጀ ሥራ አንመችም’  የሚለውን ሃሳብ ለመቀበል ራሳችንን ያዘጋጀን ይመስለኛል። ለጋራ ጥቅም ተባብረንና ተደራጅተን የመሥራት ችግራችን አሁን አሁን በሁሉም የኑሮዓችን ዘርፎች እየታየ ነው። የሽርክና ንግዶች ኢትዮጵያ ውስጥ እድሜያቸው በጣም አጭር ነው። በሃይማኖት ተቋማት እንኳን ሳይቀር መሰንጠቅ፣ አንጃና ተለጣፊ ተለምዷል። ይህ ከባድ አደጋ ነው። ለመሆኑ እንዲህ ዓይነት ችግር ያለው እኛ ዘንድ ብቻ ነው? አይደለም። የመደራጀት ችግር ሁሉም አገር ውስጥ አለ። እኛ ዘንዳ ግን በዝቷል። ማደራጀት የሥራ አመራር /ማኔጅመንት/ ክህሎት አካል ነው። የማደራጀት ብቃት ማነስ የማኔጅመንት ብቃት ማነስ አንዱ መገለጫ ነው።

በድርጅቶች ወይም በቡድኖች እድገት ውስጥ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ አምስት ዋና ዋና እርከኖች አሉ። እነርሱም 1ኛ) የምስረታ ወቅት/ Forming stage/  2ኛ) የመናጥ ወቅት /Storming stage/ 3ኛ) የመስከን ወቅት /Norming stage/ 4ኛ) የመከወን ወቅት/ Performing stage/  እና 5ኛ) የመሻሻል ወቅት/Reforming/Transforming stage በመባል ይታወቃሉ።

እነዚህ አምስት እርከኖች የግድ በዚሁ ቅደም ተከተል ይከሰታሉ ማለት አይደለም። ጉዞው ወደላይ ብቻም አይደለም ወደ ታች ማሽቆልቆልም አለ። አንድ ድርጅት በሁሉም እርከኖች ላይ የግዴታ ማለፍ አለበት ማለትም አይደለም። ቀደም ብዬ እንዳነሳሁት የመመሥረታቸው ብሥራት ተከትሎ በመጣ መናጥ የተበታተኑ ድርጅቶችን እናውቃለን። ሰፊ የሕዝብ መሠረት ከያዙ በኋላ ተንሸራተው ወደኋላ በመመለስ ተበጣብጠው የተከፋፈሉ ድርጅቶችም አሉን። የሆነ ሆኖ የኢትዮጵያ ድርጅቶችን አንድ የጋራ ባህርይ አውጣ ብባል **በመናወጥ ወቅት የሚያሳዩት እጅግ ደካማ የቅራኔ ማኔጅመንትን** ነጥዬ አወጣለሁ። በዚህም ምክንያት የመናጥን ወቅት /storming stage/ ትንሽ ዘርዘር አድርገን ብናየው ለግንዛቤዓችን ይረዳል ብዬ አምናለሁ።

የመናጥ ወቅት ስሙ ራሱ እንደሚገልፀው ድርጅቶች በቅራኔዎች የሚበጠበጡበት ወቅት ነው። በምሥረታ ጊዜ የነበረው ጨዋነት በዚህ ወቅት አይኖርም። በመስከን ወቅት እንዳለው ዓይነት በህጎችና ደንቦች መገዛት በዚህ ወቅት የለም። የጠቦች  መነሻ ምክንያቶች በጣም ብዙ መስለው ቢታዩም አስተውሎ ላጠናቸው ከአምስት መሠረታዊ ጉዳዮች ውጭ አይደሉም። እነሱም 1ኛ/ የአባላት የግል ባህሪይ 2ኛ/ የአባላት የእርስበርስ ግኑኝነት 3ኛ/ በድርጅቱ ዓላማና ግቦች ላይ የሚነሱ ጥርጣሬዎች 4ኛ/ የድርጅቱን ደንቦችና መመሪያዎችን ጥሰሃል አልጣስኩም ክርክሮች እና 5ኛ/ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በሚደረጉ ግልጽም ሆነ ስውር ግኑኝነቶች ወይም ጥርጣሬዎች ናቸው።  በመናጥ ወቅት “እነዚህ ሰዎች አብረው መሆን አይችሉም” እስከሚባል ድረስ አባላት እርስበሳቸው ላይግባቡ ይችላሉ።

ቅራኔ የእድገት ምንጭ ነውና “መናጥ” የግድ መጥፎ ነገር አይደለም። ሆኖም መናጥ ወደ ተሻለ ውጤት እንዲያመራ ሁለት ቅደመ-ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው። እነዚህም ጊዜ እና ጥበብ ይሰኛሉ።  የረጋ ወተት ቅቤ እንደሚወጣው ሁሉ የተደራጀ ደንብና መመሪያ ያላቸው እና ድርጅታዊ ባህልን ያዳበሩ ድርጅቶች ቢናጡ የበለጠ ተጠናክረው ሊወጡ እንደሚችሉ ተስፋ ማድረግ ይቻላል። ተኩስ ወተት ቢናጥ ምን ይወጣዋል? ድርጅቶችም (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## እስከዛሬ ድርጅቶቻችን ውጤታማ ለምን አልሆኑም? ከገጽ 3 የዞረ

እንደተቋቋሙ ከተናጡ መፍረሻቸው ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ቅድመ ሁኔታ “ጥበብ” የተሰኘው ሲሆን በተለይም የቅራኔ አፈታት ጥበብን ይመለከታል። ይህ ጥበብ በትምህርትና ስልጠና ሊጎለብት ቢችልም ባህላዊ ገጽታው የጎላ ነው። እኛ በትምህርትና ስልጠናችን ጎደሎነት ይሁን በባህላችን (ለምሳሌ ዘራፍ! ካፈርኩ አይመልሰኝ) ወይም በሁለቱም ምክንያቶች አላውቅም የቅራኔ አፈታት ክህሎታችን በጣም ዝቅተኛ ነው። ይህ ክህሎት ደግሞ በዘመናዊውና ከተሜው ትውልድ ዘንድ የባሰ አሽቆልቁሏል። በዚህም ምክንያት ድርጅቶች የማዕበሉን ወቅት መሻገር አቅቷቸው ተደነቃቅፈውና ተሽመድምደው ይቀራሉ። የአርባ አመታት የኢትዮጵያ የፓለቲካ ድርጅቶች ታሪክ ባጭሩ የሚከተለው ይመስላል

*እከሌ የሚሉት ድርጅት ተወለደ፣ አደገ፣ ገነነ። የእከሌ ድርጅት*

*መሪዎች ተጣሉ። እረ እንዲያውም ተከፋፈሉ። እከሌ ድርጅት*

*ደከመ። አሁንስ አለ አይባልም ነፍሱ ግን አልወጣችም ።*

ክብራትና ክቡራን ወያኔስ? ትሉ ይሆናል። የወያኔ ታሪክ ከሌሎቹ የባሰ ነው። ወያኔ በተደጋጋሚ በቅራኔ የታመሰ ሲሆን ከእያንዳንዱ መታመስ በኋላ ክፋት እያሸነፈ የወጣበት ድርጅት ነው። በ1970 ዎቹ በደረሰበት ኃይለኛ መናጥ ሲቪክ ባህሪውን አጥቶ በጥቂት ሰዎች ወደሚመራ የማፍያ ድርጅትነት ዘቅጧል። ወያኔ አንዴም መናጦችን በሞገስ ተወጥቶ አያውቅም። የመናጥን ወቅት በክብርና በሞገስ የተወጣ አንድም ኢትዮጵያዊ የፓለቲካ ድርጅት የለም።

**ክብራትና ክቡራን**

ከላይ በአጭሩ እንደገለጽኩት ድርጅቶችን ሲበጥበጡና ሲያፈርሱ የቆዩ መሠረታዊ ምክንያቶች በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች መመደብ ይቻላል።

1. የግለሰብ አባላት በተለይም የፓርቲ መሪዎች ተክለ ሰውነትን /personality/ የተመለከቱ ጉዳዮች፤
2. የአባላት የእርስ በርስ ግኑኝነት ማለትም የሳይኮ-ሶሻል ጉዳዮች፤
3. የድርጅቱን ርዕይ፣ ተልዕኮና ግብ የተመለከቱ ጉዳዮች፤
4. የድርጅቱ ደንቦች፣መርሆዎችና አፈፃፀማቸውን የተመለከቱ ጉዳዮች፤ እና
5. የውጭ ግኑኝነት ማለትም ድርጅቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ሊኖረው ስለሚገባው ግኑኝነት በተመለከተ የሚነሱ ቅራኔዎች ናቸው።

በጣም በአጭሩ እያንዳንዱን በየተራ እንድናያቸው ፍቀዱልኝ።

ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል

### የአዲስ አበባ ከተማ ታክሲ ተራ አስከባሪዎች የሰሞኑ የወያኔ ካድሬዎች ኢላማ ሆነው መሰንበታቸው ታወቀ

የዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ካድሬዎች ከምርጫው ተውኔት ጋር በተያያዘ በዜጎች ላይ የሚያደርጉትን ጫና ቀጥለው፤ ሰሞኑን ደግሞ የአዲስ አበባ የታክሲ ተራ አስከባሪዎች ተራ መሆኑን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈው መረጃ አሳውቋል።

ካድሬዎቹ በጠሩት ስብሰባ ላይ የተገኙት የታክሲ ተራ አስከባሪዎች በማንኛውም የተቃዋሚ ድርጅት እንቅስቃሴ ላይ እንዳይሳተፉ የታዘዙ ሲሆን፤ ወያኔን ለመምረጥ ቃል እንዲገቡም ተደርገዋል። ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንዳንድ የስብሰባው ተካፋዮች፤ ጭራሹኑ በምርጫው ለመሳተፍ እንዳልተመዘገቡ ግልጸውለታል።

በትግራይ ክልል የኤርትራን ቴሌቪዥን ማየት የተለመደ መሆኑ ታወቀ በቅርቡ በትግራይ ክልል ጉብኝት አድርገው የተመለሱ የአዲስ አበባ ምንጫችን ባደረሱን መረጃ፤ ወያኔ የብቻዬ በሚለው በዚህ ክልል ሳይቀር ለአማራጭ መረጃ ያለው ጥም ከፍተኛ ነው።

እንደ ምንጫችን መረጃ፥ ፖሊሶችን ጨምሮ በክልሉ ነዋሪዎች እና የመንግስት ሰራተኞች ዘንድ የኤርትራን ቴሌቪዝን መመልከት የተለመደ ነው።

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአገር ውስጥ ያሉ ነፃ ህትመቶችን በማፈን አብዛኞችን ያስወገደ ሲሆን፤ በውጭ አገር የሚገኙ እና እንደ አሜሪካ ድምጽ ራድዮ ያሉ ገለልተኛ የመረጃ ምንጮችንም እንደሚያፍን ማመኑ ይታወሳል። የኢትዮጵያ ህዝብ ንብረት የሆኑት፤ ነገር ግን በወያኔ ህገ-ወጥ ቁጥጥር ስር የሚገኙት የኢትዮጵያ ሬድዮ፣ ቴሌቪዥን እና ጋዜጦች የአገዛዙ የውሸት ማሰራጫ ጣቢያዎች መሆናቸው ይታወቃል።

### የዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ካድሬዎች በዜጎች ላይ ጫና ማድረጋቸውን እንደቀጠሉ መሆኑ ታወቀ

የዘረኛው አምባገነን አገዛዝ ካድሬዎች የወያኔን የፍርሃት እና የአፈና ምህዳር ለማስፋፋት ከቤት ወደ ቤት እየተዘዋወሩ በዜጎች ላይ ጫና ማድረጋቸውን እንደቀጠሉ መሆኑ ታወቀ።

የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ፥ ዜጎች በመጪው የምርጫ ተውኔት ማንን እንደሚመርጡ ካድሬዎቹ እንደሚጠይቁ እና ምላሻቸውን እና ስማቸውን እንደሚመዘግቡ ለማወቅ ተችሏል። በጉዳዩ ላይ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው ግለሰቦችም፥ ይህ አይነቱ ጫና የመታፈን ስሜት እንዲሰማቸው እያደረጋቸው እንደሆነ ገልጸዋል።

ወያኔ አስቀድሞ ውጤቱን በወሰነው ምርጫ ላይ እንኳ መተማመን አቅቶት ዜጎችን ማሰር፣ መግደል እና ማንገላታቱን መያያዙ፣ ያለበት ከፍተኛ ፍርሃት እና በራስ አለመተማመን ነጸብራቅ ነው ሲሉ በርካቶች ይገልጻሉ።

### የመድረክ ፓርቲ እጩ የሆኑ ግለሰብ ቤት ላይ ቦምብ መወርወሩ ተዘገበ

በትግራይ ክልል የመድረክ ፓርቲ እጩ በሆኑ ግለሰብ ቤት ላይ ሁለት ቦምቦች መወርወራቸውን አቡጊዳ የተባለው ለፓርቲው ቅርበት ያለው የዜና ድረ-ገጽ ሚያዝያ 20 ቀን ባወጣው ዘገባ አስታውቋል።

እንደ ድረ-ገጹ ዘገባ አያሌው በየነ የተባሉት ኢትዮጵያዊ፣ አቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስ በወያኔ ታጣቂዎች በተገደሉበት ሰሞን ተደብድበው ኖሯል። አሁን ደግሞ በመኖሪያ ቤታቸው ላይ ሁለት ቦምቦች ተወርውረው አንዱ ሲፈነዳ ሌላው መክሸፉን ዘግቧል። አቡጊዳ በቦምቡ ፍንዳታ በንብረት ላይ ጉዳት ከመድረሱ በስተቀር፣ በሰው ህይወት ላይ የደረሰ ጉዳት ስለመኖሩ እንደማይታወቅ ገልጿል።

የመጪው ወር የምርጫ ተውኔት በተቃረበ ቁጥር ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ላይ የሚያደርገውን ጥቃት እያፋፋመ ሲሆን፤ ከፍተኛ አመራሮችን ማስፈራራቱንም እንደቀጠለ ነው። የኦሮሚያ ፖሊስ በዚሁ ሳምንት ባወጣው መግለጫ በተወሰኑ የመድረክ አመራሮች ላይ ክስ እንደሚያደርግ አስታውቋል። ለዚህም እንደ ምክንያት ተደርጎ የቀረበው፥ በቅርቡ በወያኔ ታጣቂዎች በተደረገባቸው ድብደባ ምክንያት የሞቱት አቶ ቢያንሳ ዳባ፣ ወያኔ እንደሚለው በበሽታ ምክንያት ነው የሞቱት የሚለውን ውሸት አለመቀበላቸው ነው።

### ፕሮፌሰር መስፍንን ጨምሮ አስራ ሁለት ሰዎች በአንድነት ፓርቲ ጽህፈት ቤት ግቢ ውስጥ ከተቀሰቀሰ ረብሻ በኋላ መታሰራቸው ተዘገበ

እሮብ እለት በአዲስ አበባ በሚገኘው የአንድነት ፓርቲ ጽህፈት ቤት በተነሳ ጸብ አስራ ሁለት ሰዎች መታሰራቸውን አሶሲየትድ ፕሬስ የተባለውን የዜና አገልግሎት ጨምሮ በርካታ ድረ-ገጾች ዘግበዋል።

ከተለያዩ ምንጮች እንደተገኘው ዘገባ፥ ጸቡ የተነሳው ከፓርቲው መከፋፈል በኋላ የተፈጠረው አንድ ቡድን የፓርቲውን ንብረት ለመረከብ ወደ ጽህፈት ቤቱ መሄዱን ተከትሎ በተፈጠረው አለመግባባት ነው። አውራምባ ታይምስ የተባለው ጋዜጣ ሐሙስ እለት በድረ-ገጹ ላይ ባወጣው ዘገባ ከታሰሩት አስራ ሁለት ሰዎች መካከል አንዱ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም እንደነበሩና በዋስም እንደተለቀቁ ዘግቧል።

በአንድነት ፓርቲ ውስጥ የተፈጠረው መከፋፈል በኢትዮጵያ ነፃነት እና ዴሞክራሲ እንዲሰፍን በሚፈልጉ ወገኖች ዘንድ ከፍተኛ ውዝግብን ፈጥሮ ቆይቷል። እሁድ ሚያዝያ 17 ቀን የኢትዮጵያ ወቅታዊ ጉዳዮች መወያያ መድረክ ለሚባለው መገናኛ ብዙሃን ቃለ-መጠይቅ የሰጡት የግንቦት 7 ንቅናቄ አመራር አባል አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በጉዳዩ ላይ ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ ኢትዮጵያውያን ገንቢ ካልሆኑ የፖለቲካ ጭቅጭቆች በመቆጠብ በመሰረታዊ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ጥሪ ማቅረባቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

አቶ አንዳርጋቸው ጨምረውም፥ በኢትዮጵያ እውነተኛና ዘላቂ የሆነ አዎንታዊ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉ ዜጎች ሁሉ በግለሰቦች ላይ ካተኮሩ አተካራዎች እራሳቸውን ነፃ በማድረግ፤ በህዝብ ትግል የተገኘውን የዲሞክራሲ ጭላንጭል ሙሉ በሙሉ አሟጦ የገደለውንና አገራችንን ለከፋ ችግር እንዲሁም የመበታተን አደጋ የዳረገውን የወያኔ አገዛዝ ለመጣል በሚደረገው ትግል ላይ መረባረብ ይኖርባቸዋል በማለት መክረዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org